16ኛ ዓመት ቁጥር 91 አሶሳ
ነሐሴ 2002 ዓ.ም

# አዋጅ ቁጥር 91/2002ዓ/ም

## ከሀላፊነት ለተነሱ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ከፍተኛ ሀላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች የሚያገኙዋቸውን መብቶችና ጥቅሞች ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ከፍተኛ ሀላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች ሕዝባዊ አደራ በመሸከም ለክልሉ ሐዝብ ጥቅም የሚሰሩ በመሆናቸው ከሀላፊነት ሲነሱ ከጉስቁልና የራቀ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግና ለጥቃት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ጥበቃና ከለላ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች በኃላፊነት በነበሩበት ወቅት ያካበቱትን ዕውቀትና ልምድ ለመጠቀም አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ስለሚያስፈልግ በሥራ ላይ ያሉ የክልል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች ፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች ለወደፊት ኑሯቸው ሳይሰጉ ለክልሉ ልማትና □ድገት በቅንነት፣ በታማኝነትና በትጋት እንዲሰሩ ማበረታታት አስፈላጊ በመሆኑ በተሸሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ 49(3)(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከኃላፊነት ለተነሱ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች ፣ የምክር ቤት አባላትና ዳኞች መብቶችና ጥቅሞች አዋጅ ቁጥር 91/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

2.1. "ክልል" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማለት ነው፤

2.2. "የክልሉ ህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል" ማለት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር፣ የቢሮ ኃላፊዎች፣ የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች፣የወረዳ አስተዳዳሪዎች ንዑስ ምድብ አባል ማለት ነው፤

2.3. "የክልሉ ህግ አውጪ ምድብ አባል" ማለት የክልሉ አፈጉባኤ፣ ምክትል አፈ-ጉባኤ፣የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና የምክር ቤት አባል ንዑስ ምድብ ማለት ነው፤

2.4. "የክልሉ ህግ ተርጓሚ ምድብ አባል" ማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ዳኞች ንዑስ ምድብ ማለት ነው፤

2.5. "የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ ማለት የክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማለት ነው፤

2.6. "የቢሮ ኃላፊዎች ንዑስ ምድብ " ማለት ቢሮ ሀላፊ፣ የዞን ዋና አስተዳደሪና በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎችን ይጨምራል፤

2.7. ''የምክትል ቢሮ ኃላፊዎች ንዑስ ምድብ'' ማለት ምክትል ቢሮ ኃላፊ፣ የዞን ምክትል አስተዳዳሪና በተመሳሳይ ደረጃ የሚገኙ ኃላፊዎችን ይጨምራል፤

2.8. "በተመሳሳይ ደረጃ" ማለት በየደረጃው የሚገኙ እንደ ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር፣የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ አማካሪዎች፣ የዋና ኦዲት መ/ቤት

ኃላፊዎች፣ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎችና የመሳሰሉትን የሚጨምር ሆኖ ለአፈጻጸም ይረዳ ዘንድ ዝርዝራቸው በደንብና በመመሪያ ይወሰናል፤

**2.9.** ''የወረዳ አስተዳዳሪ ንዑስ ምድብ'' ማለት የወረዳ አስተዳዳሪ፣የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪና የወረዳ ካቢኔ  ማለት ነው፤

**2.10.** ''የምክር ቤት አባላት ንዑስ ምድብ'' ማለት የክልል ምክር ቤት አባላት፣ የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አባላት፣የብሄረሰብ ዞን የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ የወረዳ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ፣ የወረዳ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና የወረዳ ምክር ቤት አባል ማለት ነው፤

**2.11.** "የአፈ-ጉባኤ ንዑስ ምድብ" ማለት የክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ነው፤

**2.12.** "ምክትል አፈ-ጉባኤ ንዑስ ምድብ"  ማለት የክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ማለት ነው፤

**2.13.** ''የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ንዑስ ምድብ'' ማለት የክልሉ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ የብሄረሰብ ዞን ምክትል አፈ-ጉባኤና የወረዳ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ማለት ነው።

**2.14.** "የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ " ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና  ምክትል ኘሬዚዳንት ይጨምራል፤

**2.15.** "የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ ዳኛ" ማለት የክልሉ ከፍተኛ አርት ቤት ዳኛና የወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ማለት ነው፤

**2.16.** "የወረዳ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ ዳኛ" ማለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛና የሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛ ነው፤

**2.17.** "ዳኛ" ማለት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛ፣የሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛ ማለት ነው፤

**2.18.** "ባለመብት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡ መብቶችና ጥቅሞችን በመገኘት ላጁ ጸለ □ጁም ለማ□ኘት ብቁ የሆነ የክልሉ መንግሥት የክልሉ ህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል ወይም የክልሉ ህግ አውጪ ምድብ አባል ወይም የክልሉ ህግ ተርጓሚ ምድብ አባል ነው፤

**2.19.** "ቤተሰብ" ማለት የአንድን ባለመብት የትዳር ጓደኛና ሃያ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ልጆቹን ያጠቃልላል፤

**2.20.** "ተተኪ" ማለት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡

**2.21.** ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

**2.22.** ''አንድ የምርጫ ዘመን'' ማለት አምስት ዓመት ማለት ነው፤

**2.23.** ''ከኃላፊነት የተነሳ" ማለት በጥፋት ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ማናቸውም ምክንያቶች የተነሳ ባለመብት ማለት ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ከሀላፊነት የተነሳ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል
## መብትና ጥቅም

**አንቀጽ 3 የጡረታ መብት**

1/ አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ በሌላ አኳኋን የተደነገገው ቢኖርም፣ ቢያንስ አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን እና ከዚያ በላይ ጸቶለቶለ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ከኃላፊነት ሲነሳ ዕድሜው ሃምሳ ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ የአገልግሎት ጡረታ  አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

ለ) በሕመም ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የሕመም ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልኩ ይከፈለዋል፤

ሐ) በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ለተተኪዎቹ የጡረታ አበል ይከፈላል።

2/ ከአንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያነሰ ያገለገለ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ከኃላፊነት ሲነሳ 50 ዓመት የሞላው ከሆነ የአገልግሎት ዳረጎት ይከፈለዋል፤

ለ) በሕመም ምክንያት ከሀላፊነት ከተነሳ የሕመም ዳረጎት ይከፈለዋል።

3/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚፈጸሙ ክፍያዎች መጠን የሚወሰነው አግባብ ባላቸው የጡረታ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል።

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋገዎች አፈጻጸም በጡረታ ፈንዱ ላይ የሚያስከትለው የፋይናንስ ተጽእኖ በክልሉ መንግሥት ይሸፈናል።

**አንቀጽ 4 የመቋቋሚያ አበል**

1/ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከአንድ ምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ፣ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብና ለምክትል ቢሮ ንዑስ ምድብ አባል

የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የሁለት ወር ደመውዝ እየታከለ ይታሰባል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አንድ የወረዳ አስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል አንድ የምርጫ ዘመን ያገለገለ የሁለት ወር ደመወዝ፣ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ እና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ የሶስት ወር ደመወዝ ፣ ሁለት የምርጫ ዘመን እና ከዚያ በላይ ካገለገለ የአራት ወር ደመወዝ የመቋቋሚያ አበል ይከፈላዋል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከፈለው ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያ ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 5. የሥራ ስንብት ክፍያ

1/ ከኃላፊነት የተነሳ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለዋል፡፡ሆኖም ግን ክፍያው የሚፈጸመው ወደ መንግስት ስራ የማይመለስ ከሆነ ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው ወር ደመወዝ አንድ ሦስተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡ ሆኖም የሚከፈለው ጠቅላላ የሥራ ስንብት ክፍያ ከአንድ ዓመት ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 6. የመኖሪያ ቤት አበል**

1/ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከአንድ ምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ርዕሰ መስተዳድር ወይም ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ሲሆን መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) የምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከፈለው ክፍያ የወረዳ አስተዳድር ንዑስ ምድብ አባላትን አይመለከትም፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከፈለው ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያ ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡

**አንቀጽ 7. □ተሸከርካሪ አበል**

1/ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከአንድ ምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ገዜ □የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ርዕሰ መስተዳድር ወይም ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ሲሆን መነሻው የስድስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) የቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ሲሾም መነሻው የሦስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሐ) የምክትል ቢሮ ኃላፊ ወይም በተመሳሳይ ደረጃ ላይ መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከፈለው ክፍያ የወረዳ አስተዳድር ንዑስ ምድብ አባላትን አይመለከትም፣

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚከፈለው ጠቅላላ የተሽከርካሪ አበል ክፍያ ከአሥራ ስምንት ወር መብለጥ የለበትም።

**አንቀጽ 8. የሕክምና አገልግሎት**

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ለ) የሕክምና ቦርድ በሚሰጠው ማስረጃ ውጭ አገር በመንግሥት ወጪ መታከም ይችላል፡፡

ሐ) ከኃላፊነት የተነሳ ርዕሰ መስተዳድር ወይም ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ለራሱና ለባለቤቱ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝቶ ለመታከም የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል፡፡

2/ ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ  የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

3/ ከኃላፊነት የተነሳ የምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም የህክምና አገልግሎት በነፃ ያገኛል፡፡

4/ ከኃላፊነት የተነሳ የወረዳ አስተዳዳሪ ንኡስ ምድብ አባል ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም የህክምና አገልግሎት በነፃ ያገኛል፡፡

## አንቀጽ 9. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት

1/ ማንኛውም የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

2/ የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 10 የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የክልሉ የህግ የአስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዛ በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ሐ) አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

መ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣ ይሰጠዋል፡፡

2/ ከኃላፊነት ለተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ለቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል፣ለምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባልና ለወረዳ አሰተዳዳሪ ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይፈርማል፡፡

3/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ የክልሉ ህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል ፣

ሀ) በመንግሥት ሆስፒታሎች ለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ቅድሚያ ያገኛል፤

ለ) በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል፡፡

4/ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአይሮፕላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃምሳ በመቶ በመንግሥት ይሸፋንለታል፡፡

5/ የሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል እና አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተፌ ማሪ፣

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአይሮፕላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ በመንግሥት ይሸፋንለታል፡፡

6/ የሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ አሥር በመቶ በመንግሥት ይሸፋንለታል።

7/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከሀላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል □ጁም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

8/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል ቢሮ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ ሰርቪስ ፓስፖርት ይሰጠዋል።

9/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው ጥቅም ይሰጠዋል።

10/ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የወረዳ አስተዳዳሪ ንዑስ ምድብ አባል ሙሉ የነጻ የህክምና፣ ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የወረዳ አስተዳዳሪ ንዑስ ምድብ አባል አንድ ሁለተኛ የነጻ የህክምና፣ ሶስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የወረዳ አስተዳዳሪ ንዑስ ምድብ አባል አንድ ሶስተኛ የነጻ የህክምና አገልግሎት በክልሉ የመንግስት ጤና ተቋም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ከተመለከተው በተጨማሪ ያገኛል።

11/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የወረዳ አስተዳድር ንዑስ መድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተመለከተውን ዓቅም ብቻ ያገኛል፡፡

**አንቀጽ 11.የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**

1/ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

2/ ማንኛውም የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

3/ ማንኛውም የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል።

4/ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም።

5/ የወረዳ አስተዳዳሪ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተመለከተውን ጥቅም አያገኝም።

**ክፍል ሦስት**
**ከኃላፊነት የተነሳ የህግ አውጪ**
**ምድብ አባል መብትና ጥቅም**

**አንቀጽ 12. የጡረታ መብት**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ከሀላፊነት ስለተነሱ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል የጡረታ መብት የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ በደመወዝ ለሚሰሩ የህግ አውጪ ምድብ አባል ተፈጻሚ ይሆናል።

2/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የጡረታ ሕ□ ለ"መንግሥት ሠራተኛ" የተሰጠው ትርጓሜ የህግ አውጪ ምድብ አባልን ይሸፍናል፡፡

## አንቀጽ 13. የመቋቋሚያ አበል

1/ ማንኛውም የህግ አውጪ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን አገልግሎ ከ□ላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከአንድ ምርጫ ዘመን ግማሽ ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ(2)ከኃላፊነት ስለተነሱ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል የመቋቋሚያ አበል የተደነገገው ከሀላፊነት ለተነሱ የአፈ ጉባኤ ንዑስ ምድብና ለምክትል አፈጉባኤ ንኡስ ምድብ አባል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ(3)ከኃላፊነት ስለተነሱ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል የመቋቋሚያ አበል የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ የቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ንኡስ ምድብ አባል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ አንድ ደመወዝ የማይከፈለው የክልል ምክር ቤት አባል አንድ የምርጫ ዘመን አጠናቆ ከኃላፊነት ሲነሳ የክልል ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የሚያገኘውን የአንድ ወር ደመወዝ ያክል ክፍያ በዳረጎት መልክ ይሰጣዋል፣

5/ አንድ ደመወዝ የማይከፈለው የብሄረሰብ ዞንና የወረዳ ምክር ቤት አባል አንድ የምርጫ ዘመን አጠናቆ ከኃላፊነት ሲነሳ የሚገኝበትን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የሚያገኘውን የአንድ ወር ደመወዝ ያክል ክፍያ በዳረጎት መልክ ይሰጣዋል፣

## አንቀጽ 14. የሥራ ስንብት ክፍያ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ከኃላፊነት ስለተነሱ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል □ሥራ ስንብት ክፍያ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሱ ደመወዝ ለሚከፈላቸው የህግ አውጪ ምድብ አባል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20

መሠረት ወደቀድሞ ሥራው የሚመለስ የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል የሥራ ስንብት ክፍያ አያገኝም፡፡

**አንቀጽ 15. የመኖሪያ ቤት አበል**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ከሀላፊነት ስለተነሱ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል የተደነገገው ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ቶባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ከሀላፊነት ስለተነሱ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የመኖሪያ ቤት አበል የተደነገገው ለክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈጉባዔና ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) ከኃላፊነት ለተነሱ የምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የመኖሪያ ቤት አበል የተደነገገው ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

4/ ቢያንስ አንድ የምርጫ ዘመን ያገለገለ የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የስራ ጊዜ ከሚጠናቀቅበት የመጨረሻ ቀን አንስቶ ለሦስት ወር ያክል የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

**አንቀጽ 16. የተሽከርካሪ አበል**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) ከኃላፊነት ለተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል የተደነገገው ለክልል ምክር ቤት አፈጉባዔ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (ለ) ከኃላፊነት ለተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የተሽከርካሪ አበል የተደነገገው ለምክትል አፈጉባዔ እና ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሐ) ከኃላፊነት ስለተነሳ የምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የተሽከርካሪ አበል ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 17. የሕክምና አገልግሎት**

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 ከኃላፊነት ለተነሳ ለርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ለክልሉ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2 ከኃላፊነት ለተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ለክልሉ ምክትል አፈጉባዔና ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 3 ከኃላፊነት ለተነሳ የምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል የሕክምና አገልግሎት የተደነገገው ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 18. የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት**

በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 19. የመጓጓዣና የጓዝ ማጓሻ አበል**

1/ ማንኛውም ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ ምክትል አፈ ጉባኤ  የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ እና የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የሥራ ዘመኑ አብቅቶ ወደ ቋሚ መኖሪያው ሲመለስ ለራሱና ለቤተሰቡ የመጓጓዣና የጓዝ ማጓሻ አበል በወቅቱ የትራንስፖርት ተመን መሠረት ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የመጓጓዣ አበል እንዲከፈለው የየብስ ትራንስፖርት መጠቀም አለበት፤ ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥመው የአየር ትራንስፖርት መጠቀም ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የጓዝ ማጓሻ ወጪ አበል እንደሚጓጓዝበት የየብስ ትራንስፖርት ዓይነት ለአባሉ ብቻ የ1,000 ኪሎ ግራም፣ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ከሆነ ደግሞ የ1,500 ኪሎ ግራም እና ለእያንዳንዱ ልጅ 100 ኪሎ ግራም ተጨማሪ ሂሳብ ይሆናል፡፡

4/ አባሉ በግል መኪናው የሚጠቀም ከሆነ የመኪናው ነዳጅ ወጪ በኪሎ ሜትሩ ርቀት መሠረት በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

**አንቀጽ 20. የሥራ ምደባ**

1/ ከመመረጡ በፊት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ሠራተኛ የነበረ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣ የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ እኛ የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ከኃላፊነት ሲነሳ ወደቀድሞ ሥራው ለመመለስ ከጠየቀ መንግሥት ከተስማማ ወደ ሥራው እንዲመለሱ ወይም □ቀትሞ □ሥራ ቦታው ክፍት ካልሆነ በተመሳሳይ የሥራ ቦታ ላይ እንዲመደብ ያደርጋል፡፡

2/ ከኃላፊነት የተነሳው የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ እና የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ቀድሞ በነበረበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ሊመደብ ካልቻል በሌላ የመንግሥት መሠሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት በሚገኝ ተመሳሳይ ክፍት የሥራ ቦታ ላይ ሊመደብ ይችላል፡፡

3/ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣የክልል ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ፣የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤና የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በምክር ቤቱ ውስጥ ያገለገለበት ዘመን በተመደበበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ውስጥ እንደተሰጠ አገልግሎት ይቆጠርለታል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች በሹመት የሚያዙ ቦታዎችን በሚመለከት ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## አንቀጽ 21. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የምክር ቤት አባል፣

ሀ) ሁለት የምርጫ ዘመን ወይም ከዛ በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ለ) ከአንድ የምርጫ ዘመን በላይና ከሁለት የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ሐ) አንድ ሙሉ የምርጫ ዘመን ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

መ) ከግማሽ የምርጫ ዘመን በላይና ከአንድ የምርጫ ዘመን በታች ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ይሰጠዋል፡፡

2/ ከኃላፊነት ለተነሳ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባዔ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር፣ የክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤና የክልሉ ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በአፈ ጉባኤው እና የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በብሄረሰብ ዞኑ ዋና አስተዳዳሪ እንዲሁም የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በብሄረሰብ ዞኑ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ይፈርማል።

3/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባል ስለሚጸኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገጉት ለክልል ምክር ቤት አፈጉባዔ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

4/ □አገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ አባል ስለሚጸኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ የክልሉ ምክር ቤት ምክትል አፈጉባዔ ና ለብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

5/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ምክትል የቢሮ ኃላፊ ስለሚጸኛቸው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ተፈጻሚ ይሆናል።

6/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የህግ አስፈጻሚው ምድብ አባል ስለሚጸኛው ጥቅሞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገጉት ከኃላፊነት ለተነሳ ማንኛውም የምክር ቤት አባልም ተፈጻሚ ይሆናል።

## አንቀጽ 22. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

1/ ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

2/ ማንኛውም የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ እንዲሁም የክልል ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢና የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ከሀላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

3/ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በሥራ ላይ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የክልሉ መንግስት ባለስልጣን በቀበሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥር□ቱ በቀብር አስፈጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል።

4/ የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ የክልል ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ፣የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ፣ የብሄረሰብ ዞን ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ እና የወረዳ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አጸ□ር□ም።

## ክፍል አራት

## ከኃላፊነት የተነሱ የህግ ተርጓሚ ምድብ አባል መብቶችና ጥቅሞች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ከሀላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት

**አንቀጽ 23. ጠቅላላ**

የዚህ ንዑስ ክፍል ድንጋጌዎች በጡረታ ምክንያት ከኃላፊነት ለተነሱ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፐሬዚዳንትና ምክትል ፐሬዚዳንት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

**አንቀጽ 24. የጡረታ መብት**

ከኃላፊነት የተነሱ ዳኞች ጡረ□ □ሚጸቶኙት አግባብ ባለው የጡረታ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 25. የመቋቋሚያ አበል**

1/ ማንኛውም የጠቅለይ ፍርድ ቤት ፐሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ሁለት ዓመት ከስድስት ወር ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት ስድስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል፡፡ ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 26. የሥራ ስንብት ክፍያ**

1/ ከ□ላፊነት የተነሳ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፐሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የሥራ ስንብት ክፍያ ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የመጨረሻው ወር ደመወዝ አንድ ሦስተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡ ሆኖም የሚከፈለው ጠቅላላ የሥራ ስንብት ክፍያ ከአንድ ዓመት ደመወዝ መብለጥ የለበትም

**አንቀጽ 27. የመኖሪያ ቤት አበል**

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ/ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ የስድስት ወር የመኖሪያ ቤት አበል ወይም፣

ለ/ ከአምስት ዓመት በላይ አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ የመጀመሪያዎቹን ስድስት ወራት ሙሉ የመኖሪያ ቤት አበል እንዲያገኝ ተደርጎ ከዚያ በላይ ለተሰጠ የአንድ አመት አገልግሎት የቤት ክራይ አበሉ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይከፈለዋል፡፡

ሐ/ ከላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ሁለት ዓመት ከ6 ወር ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ18 ወር የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም::

**አንቀጽ 28. የተሸከርካሪ አበል**

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ፣

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ሁለት ዓመት ከስድስት ወር ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከሀላፊነት ከተነሳ፣ የስድስት ወር ተሸከርካሪ አበል ይከፈለዋል::

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የተሽከርካሪ አበል በአንድ ገዜ የሚከፈል ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፡፡

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ18 ወር የተሽከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም::

**አንቀጽ 29. የሕክምና አገልግሎት**

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ) ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደ ሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፤

ለ) የሕክምና ቦርድ በሚሰጠው ማስረጃ ውጭ አገር በመንግሥት ውጪ መታከም ይችላል፡፡

ሐ) ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንትና ምክትል ፕሬዝዳንት ለራሱና ለባለቤቱ በአገር ውስጥ የጤና ተቋም ተኝቶ ለመታከም የህክምና አገልግሎት የሚሰጠው በአንደኛ ደረጃ ማዕረግ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 30 የግል ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት**

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል በኃላፊነት ላይ በነበረበት ወቅት የግል ደኅንነት ጥበቃ ይደረግለት የነበረ ከሆነ ከኃላፊነት ሲነሳም ለእሱና ለቤተሰቡ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

2/ የጥበቃ ኃይሉ ዓይነትና መጠን ጥበቃውን በሚያካሂደው አካል ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 31. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት**

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ) አስር ዓመት ወይም ከዛ በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ለ) ከአምስት ዓመት በላይና ከአስር ዓመት በታች ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ሐ) አምስት ዓመት ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት □ምስ□ር ወረቀት፣

መ) ሁለት ዓመት ከ6 ወር በላይና ከአምስት ዓመት በታች ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣ይሰጠዋል፡፡

2/ ከኃላፊነት ለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በክልሉ ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ፣ ከጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በወረዳ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ይፈረማል፡፡

3/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ከኃላፊነት የተነሳ የክልሉ ህግ ተርጓሚ አካል፣

   ሀ) በመንግሥት ሆስፒታሎች ለሚሰጠው የሕክምና አገልግሎት ቅዲሚያ ያገኛልሰ፤

   ለ) በሕዝባዊ ስብሰባዎች የክብር ቦታ ይሰጠዋል።

4/ አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

   ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

   ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

   ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃምሳ በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል።

5/ የሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ወይም የአንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሠጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ዓቅም በተፊ ማሪ፣

   ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

   ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

   ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ ሃያ አምስት በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል።

6/ □ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ ወይም አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

   ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

   ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

ሐ) በአየር የአገር ውስጥ በረራ ሲያደርግ የአየር ትኬቱ ዋጋ አሥር በመቶ በመንግሥት ይሸፈንለታል፡፡

7/ አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል ወይም ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ የከፍተኛ ፍርድ ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከተመለከተው ጥቅም በተጨማሪ፣

ሀ) ዲፕሎማቲክ ፓስፖርት ይሰጠዋል፤

ለ) በአይሮኘላን ማረፊያ የቪ.አይ.ፒ አገልግሎት ያገኛል፤

## አንቀጽ 32. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል በሥራ ላዷ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

2/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

3/ ማንኛ□ም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል በሥራ ላዷ እያለ ወይም ከኃላፊነት ተነስቶ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ዜና ዕረፍቱና አጭር የሕይወት ታሪኩ በመንግሥት ሚዲያ ይነገራል፤

ለ) ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በቀብሩ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የአበባ ጉንጉን ያስቀምጣል፤

ሐ) የቀብር ሥነ-ሥርዓቱ በቀብር አስፈጻሚዎች በኩል የሚፈጸም ሆኖ ወጪው በመንግሥት ይሸፈናል፡፡

4/ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ንዑስ ምድብ አባል ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም።

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## ከኃላፊነት የተነሳ ዳኞች መብትና ጥቅም

**አንቀጽ 33. ጠቅላላ**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(1)ለ)፣ 27(1)(ለ)፣ 28(1)(ለ) እና 32 እንደተጠበቁ ሆኖ፣ የዚህ ንዑስ ክፍል ድንጋጌዎች በጡረታ ምክንያት ከኃላፊነት ለተነሱ ለሌሎች ዳኞች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

**አንቀጽ 34. የጡረታ መብት**

ከኃላፊነት የተነሱ ዳኞች ጡረታ የሚያገኙት አግባብ ባለው የጡረ□ ሕ□ መሠረት ይሆናል።

**አንቀጽ 35. □መቋቋሚያ አበል**

1/ ማንኛ□ም ዳኛ፣

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያው የአንድ ዓመት አገልግሎት የሦስት ወር ደመወዝ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ደመወዝ እየታከለ ይታሰባል። ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአንድ የወረዳ ዳኛና ለሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚከፈለው የመቋቋሚያ አበል ለመጀመሪያ አምስት ዓመት ያገለገለ የአንድ ወር ደመወዝ፣ ከአምስት ዓመት በላይ እና ከአስር ዓመት በታች ያገለገለ የሁለት ወር ደመወዝ ፣ ከአስር ዓመት እና ከዚያ በላይ ካገለገለ የሶስት ወር ደመወዝ የመቋቋሚያ አበል ይከፈለዋል። ሆኖም ጠቅላላ የመቋቋሚያ አበል ክፍያው ከአሥራ ስምንት ወር ደመወዝ መብለጥ የለበትም።

**አንቀጽ 36. የሥራ ስንብት ክፍያ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 26 ከኃላፊነት ስለተነሳ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ን/ ምድብ አባል □ሥራ ስንብት ክፍያ የተደነገገው ከኃላፊነት ለተነሳ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 37. የመኖሪያ ቤት አበል**

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከሀላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አገልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣

የመኖሪያ ቤት አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የመኖሪያ ቤት አበል በአንድ ጊዜ የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል መነሻው የሶስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል ሲሆን መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ18 ወር የመኖሪያ ቤት አበል መብለጥ የለበትም፡፡

**አንቀጽ 38. <u>የተሽከርካሪ አበል</u>**

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ አባል፣

ሀ) ቢያንስ አምስት ዓመት አገልግሎ ከኃላፊነት ከተነሳ፣ ወይም

ለ) ከሁለት ዓመት ተኩል ያላነሰ አግልግሎ በህመም፣ በአካል ጉዳት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሌላ ምክንያት ከኃላፊነት ከተነሳ፣ የተሽከርካሪ አበል ይከፈለዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከፈለው የተሸከርካሪ አበል በአንድ ገዜ የሚከፈል ሆኖ፣

ሀ) ለ□ቅላጁ አርት ቤት ንዑስ ምድብ አባል ዳኛ መነሻው የሶስት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ለ) ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ አባል ዳኛ መነሻው የሁለት ወራት ሙሉ ክፍያ ሆኖ ከአምስት ዓመት በላይ ላለው ለእያንዳንዱ ተጨማሪ የአንድ ዓመት አገልግሎት የአንድ ወር ክፍያ አንድ ሁለተኛ እየታከለ ይሰላል፤

ሆኖም የሚሰጠው ጠቅላላ ክፍያ ከ18 ወር የተሸከርካሪ አበል መብለጥ የለበትም፡፡

## አንቀጽ 39. የሕክምና አገልግሎት

1/ ከኃላፊነት የተነሳ የጠቅላይ ፍረድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ንዑስ ምድብ አባል ለራሱና ለቤተሰቡ በአገር ውስጥ በመንግሥት የጤና ተቋም በነፃ ወይም እንደሁኔታው በግል የጤና ተቋም በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

2/ ከ□ላፊነት የተነሳ የወረዳ ፍረድ ቤት ዳኛ ለራሱና ለቤተሰቡ በክልሉ በሚገኙ የመንግስት የጤና ተቋማት በመንግሥት ወጪ የሕክምና አገልግሎት ያገኛል፡፡

## አንቀጽ 40. የአገልግሎት የምስክር ወረቀት

1/ ከኃላፊነት የተነሳ ዳኛ፣

ሀ) ከ10 ዓመት በላይ ያገለገለ ሲሆን አንደኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ለ) ከ5 ዓመት በላይ እስከ 10 ዓመት ያገለገለ ሲሆን ሁለተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

ሐ) አምስት ዓመት ያገለገለ ሲሆን ሦስተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣

መ) ከሁለት ዓመት ተኩል እስከ አምስት ዓመት ያገለገለ ሲሆን አራተኛ ደረጃ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት፣ይሰጠዋል፡፡

2/ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛና ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ይፈረማል፣

3/ ለወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛና ለሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛ የሚሰጥ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት በጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ይፈረማል፡

4/ የአገልግሎት የምስክር ወረቀት የተሰጠው ከኃላፊነት የተነሳ ማንኛውም ዳኛ በዚህ አዋጂ አንቀጽ 31 የተደነገገው እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይሆናል።

**አንቀጽ 41. የባለመብቱ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት**

1/ ማንኛውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛና የከፍተኛ ፍረድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ አባል በሥራ ላይ እያለ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ፣

ሀ) ከመሞቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ለሚመጡ ወጪዎች መሸፈኛ የሦስት ወር ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፤

ለ) ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ ሊከፈለው ይገባ የነበረው የመቋቋሚያ አበል፣ የሥራ ስንብት ክፍያ፣ የመኖሪያ ቤት አበልና የተሽከርካሪ አበል ለቤተሰቡ ይከፈላል።

2/ ማንኛውም ዳኛ ከኃላፊነት ተነስቶ ጥቅሞችን ከማግኘቱ በፊት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ከኃላፊነት ቢነሳ ኖሮ በዚህ አዋጅ መሰረት ሊከፈለው ይገባ የነበረው ማናቸውም ክፍያ ለቤተሰቡ ይከፈላል።

3/ የማንኛውም ዳኛ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት የቤተሰቡን በዚህ አዋጅ መሠረት በአገር ውስጥ የሕክምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዲቋረጥ አያደርግም።

4/ ለወረዳ ፍርድ ቤት ዳኛና ለሸሪያ ፍርድ ቤት ዳኛ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 42. የመኖሪያ ቤትና የተሽከርካሪ አበል ተመን**

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የመኖሪያ ቤት አበል ተመን የየወቅቱን የመኖሪያ ቤት ኪራይ መጠን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከፈል የተሽከርካሪ አበል ተመን የየወቅቱን የነዳጅ፣ የቅባት፣ የዘይት፣ የጥገናና ተሽከርካሪ ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ወጪዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የክልሉ መስተዳድር ም□ር ቤት በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 43. <u>መብቶችንና ጥቅሞችን የሚያሳጡ ሁኔታዎች</u>**

1/ ማንኛውም የክልሉ ህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል፣

ሀ) የመንግሥት ፖሊስዎችን፣ በመቃወሙና በነዚህ ምክንያቶች ፖሊሲዎችን ባለመፈጸሙ ወይም ባለማስፈጸሙ፣

ለ) በሥልጣኑ ያለአግባብ በመጠቀሙ፣

ሐ) የሙስና ተግባር በመፈጸሙ፣

መ) ሚስጥራዊ መረጃዎችን ላልተፈቀደለት ወገን በመግለጹ ወይም አሳልፎ በመስጠቱ፣ ወይም

ሠ) በወንጀል ወይም በከባድ ዲስፕሊን የሚያስጠይቅ ማናቸውንም ሌላ ድርጊት በመፈጸሙ፣

ምክንያት ከኃላፊነት እንዲወገድ የተደረገ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም፡፡

2/ ማንኛውም የክልል ህግ አውጪ አባል፣

ሀ) የመራጮችን አመኔታ በማጣቱ፣ ወይም

ለ) በሥነ ምግባር ብልሹነት፣

ምክንያት ከአባልነት እንዲወገድ የተደረገ ከሆነ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም።

3/ ተገቢውን ሥርዓት ሳይከተል ከኃላፊነቱ የለቀቀ የክልል ባለስልጣን ወይም የክልል መንግስት መሪ ወይም የክልል መንግሥት ኃላፊ ወይም የምክር ቤት አባል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጡትን መብቶችና ጥቅሞች አያገኝም።

## አንቀጽ 44. መብቶችንና ጥቅሞችን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተገኙ መብቶችና ጥቅሞች በሚከተሉት ምክንያቶች ይቋረጣሉ፤

ሀ) ማንኛውም ባለመብት፣

(1) ህገ መንግስትታዊ ሥርዓትን ለማፍረስ ከሞከረ፤

(2) የሐገርን ሉአላዊነት አደጋ ላይ በሚጥል ተግባር ከተሳተፈ፤

(3) የሀገር ክህደት ወንጀል ከፈጸመ፤

(4) በኃላፊነት ላይ በነበረ ጊዜ ያገኛቸውን ክልላዊና ሀገራዊ ጉዳዮች የሚመለከቱ ሚስጥራዊ መረጃዎች ካልጠበቀ፤ ወይም

(5) በክልሉ ህገ መንግሥትና በአገሪቱ ህገ መንግሥት መሠረት የተቋቋሙትን ተቋማትን ካላከበረ፤

ለ) ከኃላፊነት የተነሳ ዳኛ ከኃላፊነት ከተነሳ ከሁለት አመት በፊት በግል ጥብቅና ስራ፣በአማካሪነትና በሌላ ስራ በመቀጠር ገቢ የሚያኝ ከሆነ፤

ሐ) ከኃላፊነት የተነሳ የክልል የህግ አስፈጻሚ ምድብ አባል ሲመራው ከነበረው የመንግሥት መሥሪያ ቤት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ባለው የግል ድርጅት ወይም በየነመንግሥታዊ ባልሆነ ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት ከኃላፊነት ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ሳይሞላው ከተቀጠረ።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት መብቶችና ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት የጥፋተኛነት ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲወሰን ይሆናል።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) እና (ሐ) መሠረት መብቶችና ጥቅሞች የሚቋረጡት ባለመብቱ ጥፋተኛ መሆኑ በክልሉ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከተጣራ በኋላ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ሲወሰን ይሆናል።

4/ በዚህ አዋጅ መሠረት በተሠጠው መብት ወይም ጥቅም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መጠቀም የማይፈልግ ባለመብት ይህንኑ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት።

**አንቀጽ 45. ለአዲስ ተሿሚዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ**

1/ አዲስ ለተሾመ ወይም ለተመረጠ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ንዑስ ምድብ አባልና ለክልሉ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ንዑስ ምድብ አባል ለመቋቋሚያ ይረዳው ዘንድ የማይመለስ የሁለት ወር ደመወዝ ይሰጠዋል።

2/ አዲስ ለተሾመ ወይም ለተመረጠ ለክልሉ ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ፣ ለምክትል ቢሮ ኃላፊ ንዑስ ምድብ፣ ለክልል ምክር ቤት ምክትል አፈ ጉባኤ ንዑስ ምድብ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ ንዑስ ምድብ፣ ለመቋቋሚያ ይረዳው ዘንድ የማይመለስ የአንድ ወር ደመወዝ ይሰጠዋል።

**አንቀጽ 46. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።ሰ

**አንቀጽ 47. የተሸሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀጽ 48. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሀምሌ 1/2001 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አሶሳ

መጋቢት ------- 2002 ዓ.ም.

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት